# የኢትዮጵያ ድሆች ድምጽ
## (ዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሣ)

(“በሚሊኒየሙ ምክንያት ድሆቹን ጠራርገው ከአዲስአበባ ሊያስወጧቸው ነው፤” ማለትን አንብቤ፥ አዝኜ፥ የኔን ድምጽ የድሆቹ ድምጽ አድርጌ ወዲያውኑ የገጠምኩት።)

**ADDIS ABABA, Ethiopia --Thousands of homeless people will be moved from the capital to the countryside before next month's millennium celebration...**



**Homeless people live on a street corner, Monday, May 9, 2005 in the Ethiopian capital, Addis Ababa. (Karel Prinsloo/AP Photo)**

አሁን የሰማንያ ዓመት ሽማግሌ ነኝ፤
ያኔ በንጉሡ ዘመን ዐርባ ነበር ዓመቴ።
ጎልማሳ ነበርኩኝ ብደኽይም
እንዳሁን ያልጎበጠ ቁመቴ።

ከድህነት በቀር
አልወጣልኝም ነበር እንከን፥
በማጣቴ አዝኜ፥ አንብቼ
ምንም ብንገላታ፥ ብብከነከን።

እንደኔው በረንዳ የምታድር
አንዲት የኔ ብጤ ወጣት
አግኝቼ ወድጄ አገባኋት
እሷም ነበረች ምንም እንከን ያልወጣት።

ሰው ነንና እኛም እንደሰው
ልጅ፥ጧሪ ቢከጅለን፥
ፈጣሪ ስሙ ይመስገን
እኛንም አንድዬ ቢያድለን፥
እኛንም እንደሰው ቆጥሮ
እግዜር ሰጠን ልጆች፤
አብረውን እመንገድ ላይ
ሊለምኑ የሚዘረጉ እጆች።

ታዲያ አንድ ዘመን፥ “ጦቢያን ሊያያት”
አሉና “ትልቅ ፈረንጅ ከ ባርማዶ ይመጣል፥”
ከከተማ ውጭ ላምበረት ወስደው አጎሩን፤
አፍረውብን፥ አድርገው ቁሻሻ እንደመጣል።

ሩህሩህ ተማሪዎች እሪ ብለው ጮኸው፥
በአያሌው ዛቱ፤ ንጉሱን ተቆጡ፤
እኛን አገር ላገር የሚዞሩትን ንጉሥ፥ እኛን ሽማግሌ
ከደረት እስከ እግራቸው በሜዳልያ የተንቆጠቆጡ።
አዎን እኛን ቀይ፥ አጭር ንጉሥ እንደራሳቸው አጭር
የሆነች በትር ጨብጠው፥የፊልድማርሻል መለዮ ለብሰው
“ሉሉ” የምትባል ድንክ ውሻቸውን እፊታቸው አስቀድመው
አገር ላገር እየዞሩ፥ ዓለምን የጨረሱት አዳርሰው።

ደርግ÷ “ 'ሉሉ' ን ከሰው አስበልጠው አክብረው ቀበሯት÷
ምዕልፌት ብሮችም ዘርፌዋል ብሎ ስድብ ወንጭፎ÷
አለፈ- ዙፋናቸውን ወርሶ÷ የኢትዮጵያን ሃብት ራሱ ዘርፎ÷
በርበሬ ነጋዴውን ሳይቀር ረሽኖ÷ ሁሉን ያለምህረት ጨፍጭፎ::

ኋላም የእንግሊዝ ንግሥት ኤልዛቤጥ ኢትዮጵያ ቢመጡ÷
የንጉሱ ባለሥልጣኖች እኛን ደብቀው÷ አፍነው÷
ንግሥቲቱ ሃገራቸው ሲገቡ÷ አደነቁ አሉ ሲሉ -
“ኢትዮጵያ አንድ ድሃ የለም፤ ሁሉም ሰው ሃብታም ነው::”

ዘግይቶም÷ ለኛ ለተገፋነው÷ ለወደቅነው ሰዎች ሲባል
መጣ አሉ ሰው-በሌ አብዮት፤
ንጉሡ ቤት አንኳኩቶ ገብቶ÷
አላቸው “በመጀመሪያ እስቲ እሶን ልዮት!”

ቀጥሎም መኳንንቶቻቸውን
አንድ ባንድ ኅበኛቸው፤
ወታደሩ÷ ፖሊሱ÷ ባለቢሮው÷
ነጋዴው ሁሉ ተገልብጦ ሆነ ጠበኛቸው፤
ድሮ “የኢትዮጵያ ቤዛ÷ብርሃን”
ብሎ÷ በመሬቱ ግንባሩን እንዳልፈነከተላቸው÷
አሁን ግንባሩን እንደቀንድ አሹሎ÷ ነኝ አለ ደመኛቸው::

“ለናንተ እንዲያልፍላችሁ ነው፤” አሉንና÷
ወታደሩ መኳንንቱን ጨፍጭፎ ጣላቸው፤
ድሮ ያመልካቸው የነበረው ህዝብ÷ ክብራቸው
የማይገሰሰውን ንጉሥ “ሌባ!፡ ብሎ ተጣላቸው::

በእኛ በጭቁኖቹ ዕጣ ፊንታ ተቆርቁሮ÷
ጀመረ ተማሪው ከወታደሩ መፋለም፤
የራሱን መደብ ከድቶ÷
እኛ እንድንኖር በደስታ÷ ባለም::
መልሶ ደሞ÷ ርስበርሱ ጀመር ይፈላለጥ::
ወንድም ወንድሙን ሲያርድ÷ ሲያሳርድ÷
ግራ ገብቶን ቃኘን - ሲጠቋቆምናም ሲገላለጥ::

በንጉሡ ዘመን የደረሰብን ውርደትና
እንግልት ሳያንሰን÷ አትትረፉ ሲለን ከሽብር÷
እና ከማያባራ ስቃይ÷ ደርግ በኛ ሥም ሥልጣን ላይ
የተንፈራጠጠበትን አሥር ዓመታት ሲያከብር÷
እሱም ጠራርጎ ከከተማው አስወጣን
ህልውናችንን ከኮሙኒስት ኅብኝዎች ሰውሮ ሊቀብር::

እንደ ደርግ አዋጅ ብዛት÷ እንደ ልፈፋው ጋጋታ÷
ሲሆን ሲሆን ታላላቅ ህንጻ÷
ሳይሆን ሳይሆን ቪላ ቤቶች
መስሎን ነበር የሚታደለን በነጻ::

እንደኔው ዓይነቶቹ ነዳያን እንኳን በህንጻ÷
እንኳን በቪላ ሊቀመጡ
ወታደሮቹ የሰው ንብረት ሲነጥቁ
እስከናካቴው የኛንም በረንዳ ቋመጡ::

በኛ ሥም ያሁሉ ደም እንደ ዠማ ወንዝ ፈስሶ÷
እኛ አሁንም እዛችው እድሮዋ በረንዳ ነን፤
የደም አበላ ብዛት÷ የራዲዮ ሽለላ÷ያዋጅ ጋጋታ÷
የቁም ስቅላችንን አባሰብን እንጂ ከቶም አላዳነን::

እበረንዳ ሰፍረን ታዘብን – የከበሩት ሲደኸዩ÷
ቀን ወጥቶላቸው÷ የደኸዩት ደሞ ሲቶጅሩ÷
የጠገቡት ያብዮት አፈር ዘግነው÷
የሰው እንጀራ÷ወጥ ላይ ሲሞጅሩ::
ደሞም ዐየን በኮሙኒስት ንብረት ነጣቃ÷
አገር ሁሉ ተያይዞ ደህይቶ÷
ሢሳነው እኛን ለመመጽወት÷
ሕልቆመሳፍርቱ ራሱ በ'ጦት ተሰቃይቶ::

ዐይን ከማየት÷ ጆሮ ከመስማት አይታቀብምና÷
ለጉድ ጎልቶን ደሞም ሰማን÷ ዐየንም ለኢትዮጵያ ተገዳዳሪ
ጠላቶች÷ መብረቅ÷ መቅሰፍት የነበሩት ወታደሮች ሲለምኑ÷
ሜዳልያቸውን ደርድድረው÷ እንደኛ ሆነው በረንዳ አዳሪ::

መንግሥት መጣ፤ መንግሥት ሄደ፤
እልፍ ጡሩንብ ተነፋ÷ ተምባረቀ ሺ አዋጅ÷
እኛን ግን ከእንግልት÷ ከሥቃይ÷
ከቶም÷ ከቶም አልተገኘም የሚዋጅ፤፤

ለተዓምር አስቀምጦን÷ በቅጡ ለምነንም
እንዳንኖር÷ ሰው–በሌው አብዮት ስንቱን ሲፈነግል÷
ስንቱን ሲመነግል÷ ቀረን ሰቆቃችን ብሶ÷
ካይናችን ሲመነጭ ደምና መግል::

ዛሬ ደግሞ ይባስ ብሎ ሳለን በሃያል ጉስቅልና÷
“ሚሌኒየም” የሚባል የደላቸው ሰዎች ፌስታ÷
ወደ ኢትዮጵያ ገስግሶ መጣ፤ ብለው ጠራርገው ካዲሳባ÷
ሊያስወጡን ነው÷ እንደተውሳክ እንዳናበላሽ የነሱን ደስታ::

የሄደው የመጣው÷ የሚመጣውም ገዢ ሁላ÷
ይለፍፋል ላለም÷ እያለ አገር አሳደግን፤
ልፈፋው ሃሰት መሆኑን የኛ መኖር ይመሰክራል፤
የኛ ድህነት ያሳጣዋል÷ መንግሥት ቢያወጋ ደግ ደግን::
እኛ ነን የኋላ መቅረት መለኪያው÷
ሁሉም መንግሥት ገስግሰናል ቢልም ግን::

አፍረውብን ነው አሉ አሁንም የሚሰውሩን፥
ፈረንጅ እኛን ተጠይፎ እንዳይዘጋ ወስፋቱ::
ኧረ መቼ ነው የምንሆን የኢትዮጵያ ዜጋ፥
ከቶ መች ይሆን የሚጠብ የድህነታችን ስፋቱ?

ጎብኚዎች ዐይተውን እንዳያፍሩ፥
መንግሥቶቻችን ሁሉ ሁሌ ከሚደብቁን፥
በስማችን ከሚያካብቱት ንዋይ ምነው ቆንጥረው ቢዘከሩን?
ምናለበት ድህነታችንን ጥቂት ቀርፈው፥ ለሰውነት ቢያበቁን፥
ወቅት ወቅት እየጠበቁ፥በየዘመን አዝማናቱ፥
እንደክርፋት፥እንደቁስል ከሚያብቁን?

እናንተ ስትተኩሱ ርችት፥ ሠማዩን ከኮከብ ይልቅ ስታቅለመልሙት፥
ስትቆርጡ ጮማ፥ ስታፈነዱ ስትራጩ ሻምፓኝ፥ ስትዋኙ በውስኪ፥
"እባክችሁ ስለኢትዮጵያ ዓምላክ፥ ጥጋት፥ ውሃና ፍርፋሪ አትንሱን፥"
ብንል'ንጂ አፋችንን ምን ቆርጦን ልንል "ጮማ፥ ውስኪ ስጡን እስኪ?"

ኧረ ለመሆኑ እኛ እውነት
ነን እንዴ የሰው ልጅ ፍጡር፥
ውሻ እንኳን እቤት ተቀምጦ ሢቀለብ፥
እኛ ከውሻ በታች ተጥለን የሚደርስብን ጡር?

በኛ ስም ያ ሁሉ የደም አበላ
በኢትዮጵያ መሬት የፈሰሰ፥
ያ ሁሉ ሰው የተሠደደ፥
ያ ሁሉ ርስት፥ቤት የተወረሰ፥
ያ ሁሉ የእምባ ፏፏቴ ጉንጮችን የገማመሰ፥
ያ ሁሉ  ሕይወት የተደመሰሰ፥
እኛ እንደሁ አላለፈልን፥
ለምን ነበር ምድሩ የታመሰ፥
ድንጋዩ የተነፈነቃቀለ፥
ሠማዩስ የታረሰ?

እግዚኦ! እግዚኦ! ያንተ ያለህ!
እስከመቼ ይሆን መንግሥቶቻችን ሁሉ የሚያፍሩብን?
እግዚኦ! እግዚኦ! እስከመቼ ይሆን ሁሉም በስማችን እየለመኑብን፥
ሁሉም በተራ እኛን ይብስ አደህይተው እነሱ ሃብት የሚያፈሩብን?

የኢትዮጵያ ለማኝ ሁሉ ይላል፥"የሚያጠፉኝ መንግሥት 'ንጂ
"ከቶም የለም የሚያለማኝ::"
እባካችሁ ለምን ለማኝ ትጠላላችሁ፥
ራሳችሁ ሆናችሁ ለማኝ?
ዘላለም ትለምናላችሁ እንደኛው:: እናንተስ መቼ ነው
ኮርታችሁ፥ ቆፍጥናችሁ በላባችሁ እየኖራችሁ የምታቆሙ ልመና?
በስማችን ለምናችሁ፥ ለምናችሁ፥ የየግል ኮረጇችሁን እያሳበጣችሁ፥
ኡሁንም ትለምናላችሁ፥ ነገም ትለምናላችሁ፤ ልመናችሁ ሆኖ መና::

ነገሩን የሁላችንም አሳዳሪ ፈረንጆች ያቁታል።- እንደራሳችሁ እዩት፥
እናንተ በትልቁ እንደምትለምኑት እኛም በትንሿ እንለምን፤
እናንተ ሠፌ አቁማዳችሁን ይዛችሁ እየለመናችሁ፥
ለምን ታግዱናላችሁ እኛ በትንሿ ጥርኛችን እንዳንለምን?

እስቲ እናንተን ምን ይሰማችሁአል ተመጽዋቾቻችሁ ፈረንጆች፥
እናንተን ጠራርገው ቢያስወጧችሁ ከከተማ?
እንደዛው አስቡት ጌቶቻችን ሆይ! በናንተ ይሄ ውርደት ከደረሰማ፥
አወየው! ወየው! ሕይወታችሁ አከተማ!

ጌቶቻችን ሆይ! ባካችሁ ሥለ አንድዬ ብላችሁ፥እሱንም ካልፈራችሁ፥
ሥለምትወዷቸው ብላችሁ ተዉን፤ እኛም ከዚችው ምድር ነው የበቀልን።
ፌስታ፥  ፈንጠዝያችሁን ባካል ባንካፈለውም ባይናችን እንቅመሰው፤
ስለ ኢትዮጵያ አምላክ ተዉን! ሰው አንሆንም ከተነቀልን።

እ ኤ አ  ነሃሤ 30 2007
ቫሌሆ፥ ካሊፎርኒያ